የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራአንደኛ ዓመት ቁጥር ፴፪
አዲስ አበባ- ሚያዝያ ፳ ቀን ፲፱፻፺፯

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

11th Year No. 32
ADDIS ABABA- 28th April, 2005

**ማውጫ**

አዋጅ ቁጥር ፬፻፵፭/፲፱፻፺፯ ዓ.ም

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽንን የሂሣብ አያያዝና የክፍያ መጠየቂያ ሥርዓት ያልተማከለ ለማድረግ ለሚያስችለው ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ተጨማሪ ብድር ከኖርዲክ ልማት ፈንድ ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ..................ገጽ ፫ሺ፹፱

**CONTENTS**

**Proclamation No. 445/2005**

Nordic Development Fund Credit Agreement for Financing Decentralized Accounting and Billing system for the Ethiopian Electric Power Corporation Ratification Proclamation........ Page 3089

## አዋጅ ቁጥር ፬፻፵፭/፲፱፻፺፯

## የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በኖርዲክ የልማት ፈንድ መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽንን የሂሣብ አያያዝና የክፍያ መጠየቂያ ሥርዓት ያልተማከለ ለማድረግ ለሚያስችለው ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ፫ ሚሊዮን ኤስ.ዲ.አር. (ሦስት ሚሊዮን ኤስ.ዲ.አር) የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በኖርዲክ የልማት ፈንድ መካከል እ.ኤ.አ. ዲሴምበር ፩ ቀን ፪ሺ፬ በአዲስ አበባ የተፈረመ በመሆኑ፣

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሚያዝያ ፮ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ያፀደቀው ስለሆነ፣

በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ ፶፭(፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል::

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽንን የሂሣብ አያያዝና የክፍያ መጠየቂያ ሥርዓት ያልተማከለ ለማድረግ ለሚያስችለው ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ተጨማሪ ብድር ከኖርዲክ ልማት ፈንድ ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፬፻፵፭/፲፱፻፺፯" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

## PROCLAMATION NO. 445/2005.

## A PROCLAMATION TO RATIFY THE CREDIT AGREEMENT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE NORDIC DEVELOPMENT FUND

**WHEREAS,** a Credit Agreement, between the federal Democratic Republic of Ethiopia and the Nordic Development Fund stipulating that the Nordic Development fund provide to the federal Democratic Republic of Ethiopia additional credit in an amount not exceeding SDR 3,000,000 (three million SDR) for financing decentralized Accounting and Billing System of the Ethiopian Electric Power Corporation, was signed in Addis Ababa on 1st day of December 2005;

**WHEREAS,** the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Credit Agreement at its session held on the 14th day of April, 2005;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55 Sub-Articles (1) and (12) of the constitution, it is hereby proclaimed as follows:

**1. Short Title**

This Proclamation may be cited as the "Nordic Development Fund Credit Agreement for Financing Decentralized Accounting and Billing System for the Ethiopian Electric Power Corporation Ratification Proclamation No.445/2005"

ያንዱ ዋጋ 2·30
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፹
Negarit G. P.O.Box 80

## ፪. <u>የስምምነቱ መፅደቅ</u>

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በኖርዲክ የልማት ፈንድ መካከል እ.ኤ.አ. ዲሴምበር ፩ ቀን ፪ሺ፬ በአዲስ አበባ የተፈረመው የብድር ስምምነት NDF 198 ማሻሻያ ቁጥር 1 ስምምነት ፀድቋል::

## ፫. <u>የገንዘብና ኤኮኖሚ ልማት ሚኒስትሩ ሥልጣን</u>

የገንዘብና ኤኮኖሚ ልማት ሚኒስትሩ በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፫ ሚሊዮን ኤስ.ዲ.አር. (ሦስት ሚሊዮን ኤስ.ዲ.አር) በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል::

## ፬. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ ከሚያዝያ ፳ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል::

አዲስ አበባ ሚያዝያ ፳ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ.ም

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**
**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**
**ፕሬዚዳንት**

## 2. Ratification of the Agreement

Amendment No. 1 to the Credit Agreement NDF 198 signed in Addis Ababa on the 1st day of December 2004 between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Nordic Development fund is ratified.

## 3. Power of the Minister of Finance and Economic Development

The Minister of Finance and Economic Development is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the credit amount of SDR 3,000,000 (three million SDR) in accordance with the terms and conditions set forth in the Credit Agreement.

## 4. Effective Date

This Proclamation shall enter into force on the 28th day of April, 2005

**Done at Addis Ababa, this 28th day of April,2005**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**
**PRESIDENT OF THE FEDERAL**
**DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**